ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በ የካቲት 6 ቀን ቀን 2011 ዓም የተላለፈ ሐተታ

# የሰው ማንነቱ፤ ከሚለው ሳይሆን ከምግባሩ

ይህንን መደጋገም ባላስፈለገ ነበር ። ነግር ግን የሐሳዊዎች ዓመታት ተጭኖን ስለከረምን የነገሮች ቅጥ አምባሩ እየጠፋን፤ የኢትዮጵያዊነት ጿጋም እየተሸረሸረ፤ከህቅ እየተጣላን፤ግንዛቤያችንም እየተዛባ፤አረመኔን እያዳነቅን፤ቅሌትን አቅፈን ከርመናልና የሰው ማንነትና ምንነት ይዘቱ ተሰውሮብናል ብንል ስህተት አይደለም ። ዛሬ በወያኔዎች ሀሰት ተደናግረን ሀገራችንን ልናስረክባቸው ጫፍ ላይ መሆናችን ለዚህ ምስክር ነው ። ድሃ ተበድሎ ማሩኝ ይላል ቶሎ ያከትም ካልን ዓመትት አልፎ ዛሬ ሀገራችንን ሊቀሙ የተነሱት ክሀዲ ምሁሮች ተሰባስበው ወደ ዕልቂት እየወሰዱን ነው ። ይህንን ተንኮላቸውን አፈር አብልተን ኢትዮጵያን ማዳን ደግሞ ዋና ግዳጃችን ሆኖ ይገኛል ። ህዳጣን በወያኔ ገፋፊነት ከሕዝብ ጋር የሚያደርጉትም የጥላቻ ዘመቻ ውሎ አድሮ ወደ ጥፋታቸው የሚያመራ መሆኑም አይቀሬ ነው ። መክረናል በጊዜ ሰሚ ከተገኘ ።

የሰው ማንነቱ በግብሩ እንጂ ከአፉ ከልፈፋው የሚሰረጽ ወይም የሚደመደም አይደለም ። የፖለቲካ ድርጅቶች ስለራሳችው ባላቸው ግምት የሚገመገሙ ቢሆን ኖሮ ሁሉም በእውን ዴሞክራሲያዊና ለሕዝብ የሚበጁ በሆኑ ነበር ።ደርግም እኮ የሠርቶ አደሩ ሕዝብ መንግስት ነኝ ሲል መለስ ዜናዊም ከባሰችው ዋሾ ሚስቱ ጭምር ሁላችንም ልንገነባ እንጂ ሸንሽነን ልናፈርስ አልመጣንም ሲለን ነበር ። መመዘኛው ተግባር ነው።ማንነትም ከስራና ከተጨባጩ ሀቅና እውነታ የሚገኝ ነው ። ምኞትና ተስፋ ለየቅል ሆነው በረድፋቸው ስልፍ መያዛቸው እንዳለ ሆኖ ማለት ነው ። ምን ተደረገ፤ምን ተከሰተ ስንልም ከትግል አንጻር ለምንስ ታግለን፤ምን ፈልገንስ ተሰዋን ብለን መጠየቅ የግድ ይሆናል ።ንጉሱ ከሥልጣን ይውረዱ ስንል ጭቃ ሹም ጫቅሌ ከቦታው ተባሯል ምላሽ ሊሆን አይችልም ። ወያኔን ያቃወሰው ትግል፤ባዕዳንን ያስደነገጠው ትግል፤ሕዝብ ህብረቱን አጠናክሮ ደማችን አንድ ነው፤ስር ነቀል ለውጥ ይምጣ፤ሕዝባዊ መንግስት ይመስረት ሲል ያካሄደው ትግል፤ ሀገር ቅርጫ ገብታ የየድርሻችንን እንቦጭቃት በሚል አልነበረም ። ኦሮሚያ፤አማራያ፤ኦጋዴንያን ለመምስረትም አልነበረም። ወያኔ ኢሕአዴግንም ጠጋግኖና አድሶ (ጥንብን ሽቶ ረጭቶ) ለማስቀጠል አልነበረም ። ሕዝቭ ያልመረጠው ግን አሜሪክና አረቦች የሰየሙልንን ሹም አወድስን ለመቀበልም አልነበረም ። ዳግም የሻዕቢያ ሰለባ ሆኖ መሳለቂያ ለመሆንም አልነበረም ። ወነጀለጮችና ሽብርተኞች የሀገራችን የክብር እንግዳና ሹሞች ለማድረግም አልነበረም ፡፤የእነዳውድ ኢብሳ፤ሌንጮዎችና ባለሜንጫዎች ውርጋጦችም አረመኔነት መከሰቻ ለመሆንም አልነበረም ። ሕዝብ የፈለገው፤ደሙን ያፈሰሠው ለኢትዮጵያ፤ ለሕዝባዊ መንግስት፤ለወያኔን ኢሕ አዴግ ውድቀትና መንኮታኮት ነው ። ይህን የሕዝብ ፍላጎት ለማደባየት አሚውሪካ አበጥራና አጥንታ የዛሬውን ሹም መርጣ አሰለጠነች ። በፕሮፓጋንዳና አደናጋሪዎች--አሻሻጮችም--አጅባ አሰማራች። ሾመች፤አጨበጨበች፤አስጨበጨበች ። የተደናገሩ ጥቂቶች ናቸው ማለት አይቻልም ። በሆዳቸው የተገዙ ብቻ ሳይሆኑ በአጉል ተስፋ ተሳፋሪዎችም ነበሩ፤ዛሬም አሉ ። ያሳዝናል-- ነግ ሁኔታው አስቀያሚ ገጽታውን ሲያሳይ ሞራላቸው ይደቃልና፤ፖለቲካ ለአፈር ብለው ሀገራችንን የሚጎዳ ምርጫ ሊወስዱ ይችላሉና።

ለግምገማ ወይም ድጋፍና ወቀሳ ውግዘት ስንነሳ ከሀቅ መሆን አለበት ። ከተራ ጥላቻ ወይም ባዶ ምርቃና ሊሆን አይችልም፤ አይገባውም ። በድፍኑ መልኩያምራል፤ቃላቱ ይስባሉም ከሚል መሆን አይችልም ። ገለባ ግምቶች የህገርን ሁኔታ ሊገመግሙ ሊፈቅድላቸው አይገባም ። ከመሰረቱ ቀፈትን መጠርጠር አነሰን ያልነው የምጣዱ እንጀራ ሕጻንም የማያጠግብ ሆኖ ስለተገኘ ነው ። ወያኔ ኢሕ አዴግን ማስወገድ ሳይሆን ማሰቀጠል በመሆኑ፤በባዕድ የተሰየሙብን በመሆኑ፤ከባዶ ቃላት ውጪ ነፍስ ያለው ባለመሆኑ፤ዘረና በመሆኑ በተጨባጭ፤ ከመጀመሪያው ቀፈን ውሎ አድሮም አለመሳሳታችንም አረጋገጠ ። ሹሙ ለውጥ ሳይሆን የገማ የገለማውን ኮሾ ሽቶ ረጭቶና ኳኩሎ ቀጣይ መሆኑንም አረጋገጠልን ። የፖለቲካ ብስለቱም አስገማች መሆኑን በሚለፍፈው ውሸት አረጋግጧል ። የሚተቸኝ የሚቃወምኝ ድርጅትም ሆነ ራዲዮ የለም ያለው በቅርቡ በቂ መረጃ ነው ። ኢሕአፓም ፍኖተም እንዳልደገፉትና እንደ አድርባዮቹ እንዳልሰገዱለት ያውቃል ግን ሽምጥጦም መዋሸቱን መርጧል ። ውሸት ደግሞ ውሎ አድሮ ይጋለጣልና ጠቃሚነቱ ጊዜያዊ ነው ። የሹሙ ኢትዮጵያዊነት ራሱ ውሸት መሆኑ በበቂ ተጋልጧል ። የእኛ ስራ ወይ ቅስቀሳ ውጤት ሳይሆን የራሱ ስራ ያጋለጠው ነው ። ስልጣን እንደያዘ እነማንን የክብር እንግዳ ብሎ ጋበዘ ጠራ? በሞላ ጸረ ኢትዮጵያዎችን ። ማንን በብሄረሰብና በሀይማኖት መሰረት ሾሞ ሀገሪቷን ሞላ? ያለውን ሕዝብ የጠላውን ስርዓት አስቀጥላለሁ፤ሕዝብ የጠላውን ህገ መንግሥት አስጠብቃለሁ ብሎስ ለፈፈ? ራሱ ።አማራን ክርስቲያንን በሜንጫ እናርዳለን ያሉ ወርበሎችን ቤተ መንግሥት ማን አስገባ ? ራሱ ።ማን ፋሺስቱን አረመኔ መንግሥቱን ከሓራሬ ሊያስመጣ ሞከረ ? ራሱ ። ማን ሁሉንም የፖለቲካ እስረኞች መፍታት የሚለውን የህዝብ ጥያቄ አፈር አበላ?ራሱ ። ማን የሽግግር ሂደትና ጉባኤ አይፈቀድም ብሎ በኢሕአዴግ ስር ምርጫ የሚል ቧልትን አስቀደም? ራሱ ሹሙ ከነጭፍሮቹ። አይናችንን ከፍተን እስኪ እነማንን እየሾመ እያለ ነው ብለን እንመርምር። ኢትዮጵያ በገሃድ ለቅርጫ ቀርባ የምትገኘው ዛሬ ነው ። የግንጠላ ከይሲ ተኩላዎችና ጅቦች ጥርሳቸውን አግጠው ሊቦጭቋት ዕድል አግኝተዋል ። የሀገራችን ህልውና ለአደጋ ተጋልጧል ። ያለውን አስከፊ ሁኔታ አላይ ያለ ዜጋ ሁሉ የሀገሩ ውድቀት ተባባሪ ነው አሊያም ሰው ከሚያሰኘው ህሊናና እይታ ጋር ተለያይቷል ። ሲነግሩት ያልሰማ በቁሙ ሲሸለትም አይገባውም እንዳይባልብን እንጠንቀቅ።

የፖለቲካ ስልጣን ሳይዙም ፤ ሊይዙም ሲሉ ሆነ ከያዙም በኋላ ጭፍን አምባገነኖች ቃላቸው በሞላ ሀሰት ለመሆኑ ኩንታል ተመክሮ አለን ። ወጣቱ ትውልድ ፈረንጅ የሰጠንን ማዘንጊያ ነጻ አውጪ ብሎ ከመቀበሉና ከማወደሱ በፊት ይህን መረዳት መገንዘብ አከበት ። ታሪኩን ማወቅ ማጤን አለበት--ሀገር ይኖረ ዘንድ ከፈለገ፡፤ኢትዮጵያ የትግል የመስዋዕት ውጤት ናት--የስሜትና የባዶ ጫጫታ ፍሬም አይደለችም ። የሚወዷት ሊሰዉላት ድረስ ዝግጁ መሆን አለባቸው። ጠላቶችዋን ወዳጅ በውም ሊያቅፉ አይጠበቅም ። የባንዳን ሳይሆን የአርበኞችን ተምሳሌት ማስቀደም አለባቸው ። የነበላይ ዘለቀን፤ የመንግሥቱ ንዋይን፤ የነማርቆስ ሐጎስን ገዳዮች ማዳነቅም አይጠበቅባቸውም ። ኢትዮጵያ ሀገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ የሞተልሽ ሳይሆን የገደለሽ በላ ለአንዴም ለሁሌም መቀበር መጥፋት ያለበት አባባል ነው ። የግፈኛ አጼዎች፤የደርግና የመንግስቱ፤ የመለስና ጭፍሮቹ ወንጀሎች እንዳሉ ሆነው፤አሶሳ በደኖ ወዘተ ጭፍጨፋን ያዘዙ አረመኔዎች ግፍ እንዳለ ሆኖ ዛሬ ታሪክ ተከዶ ለፍርድ መቅረብ ያለባቸው ለሹመት ሲቀርቡ--በ ሹሞቹ ብሄር አባልነታቸው-- ልንቀበለው የምንችለ መሆን የለበትም።ፍትህ ለሰማዕት ። ፍርድ ለነአሰፋ ማሩ፤ለነማርቆስ ሐጎስ፤ለነተስፋዬ፤ ለስንቱ አማራና፤አኝዋክ፤ ለስንቱ ንጹህ ዜጋ ገዳዮች ማለት ይጠበቃል ። ሀገር ላጠፋ ሻዕቢያስ ማጎብደድ መለሳለስ ምን ይባላል ? እንዴትስ አማራ ገዳዩ ኢሳያስ የጎንደርን መሬት ይረግጣል ? የሹሙስ አማካሪዎች እነማን ናቸው ጸረ ሕዝቦች እንጂ ! ተጨባጩን ሁኔታ ስናጤን፤ የሚካሄደውን ከተዛባ ዕይታ አላቀን በጥሞና ስናይ ቀደም እንዳልነው ሁሉ ሹሙ ወያኔን ሊያድን ባዕዳን የሰየሙብን ጋሬጣ

እንጂ ከቶም ሌላ አይደለም። ሕዝብ ደሙን አፍሶ ያመጣውን ሁኔታ ጠልፎ ወያኔ ኢሕአዴግን ከጥፋት ሊያድን የመጣብን የባእድ ጋሪጣ ነው ። ኢትዮጵያዊነቱ ልብወለድ ነው ። ሕዝብን አዘናግቶ ሀገርን ለማሳጣት የመጣብን ዘረኛ ነው። ይህ ሀቅ ዛሬ የሀገራችን ሕዝብ እየተረዳው መጥቷል ። በባዕድ ሀገር ነዋሪ ምድረ ሀበሻ ይል እንደነበረው ዝነኛው ሀይሉ ገሞራው፤ ያፈተተውን ቢቀላምድ ይህ ሀቅ የሚሰረዝ ሊሆን አይችልም ። የሆድ አፍ የህሊናን ሀቅ መቸም አይሰረዝምና ።

አለውና አለውና በማህተቡ ጸና ይባልልን ። ዓመት ሰጥተን አየን ። ሕገራችን ወደተሻለ ሁኔታ ገባች ወይስ ዲስኩር እየተመገበች ልትጠፋና ቅርጫ ልትገባ ተሰናዳች? ታረደች ? የሀግርን ጥፋት ማጀብ ወንጀልም ሐጢያትም ነው ። ያለውን ስርዓት ማጀብ በሀገራችን ኢትዮጵያ ላይ ጥፋትንም ማጀብ ነው ። ሌላ ምንም ትርጉም የለውም ። እየተነገረው በጥፋቱ የሚቀጥል ደግሞ ያተሪክ ተወቀቃሽና የውግዘምትም ተሸካሚ ነው ። ኢትዮጵያዊ ሊባል የሚችልም አይደለም ። የተደናገሩና የተሳሣቱ ይታረሙ እንላለን ። ሕዝብ ደግሞ ከማንም ስርየትን ሳይጠብቅ ብሁልገብ ትግል ራሱንም ሀገርንም እንዲጠብቅ ጥሪ እናደርጋለን ። ስርዓቱ ጸረ ሕዝብ ነውና ባለ ዓቅም ሁሉ መታገልና መቋቋም ያስፈልጋል ። የምጡብን ያው የማናውቃቸው የጥፋት ሀይሎች ናቸውና ብህብረትና ኢትዮፕያዊነት ተነስተን በሁሉም ፈርጅ--በሁለገብ ትግል-- ታግለን ልናደባያቸው ያስፈላጋል ።የሀገራችን የኢትዮጵያ አድኑኝ ጥሪ ይህ ነው ።

ጸረ ወያኔ ኢሕአዴግ ትግላችን ተፋፍሞ ይቀጥል !!

ኢትዮጵያዊነት ያችንፋል!!

ውድቀት ለሹሞቹ ኢሕአዴግና ዘረኝነት !!!